የሰበር መ.ቁ 13223

ጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

5. አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

መልስ ሰጭ፡- አቶ አስፋው አበበ

ስለ ፍርድና ስለትዕዛዝ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ጉዳይ ውጭ ጭብጡን ለውጦ ውሳኔ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ስለሚሰጥበት ሁኔታ፡- የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 182/2/፣ 342፣345/1/ለ/

መልስ ሰጭ የጎንደር ስጋ ፋብሪካ ገንዘብ የሆነ ብር 486,312.00 የባንኩን አሰራር በመጣስ ለአምጭው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሰላ ቅርንጫፍ በኩል እንዲከፈለው በማድረግ በፈጸመው ድርጊት ከስራ ተሰናብቶ የወንጀል ጉዳዩ በሂደት ላይ የነበረ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ/ሰጭ ወደ ስራ እንዲመለስ የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ እየታየ እያለ መ/ሰጭ በፈጸመው ድርጊት በወንጀል ተጠያቂ ተደርጎ ብር 500.00 የተቀጣ ቢሆንም ይኸው ክርክር የቀረበለት ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች የወንጀል መዝገቡን በማስረጃነት አላቀረበም በሚል ክርክሩን ውድቅ ስላደረገው የቀረበ አቤቱታ፡፡



ውሳኔ፡- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያሻሻለው ውሳኔዎቹ ተሽረዋል፡፡

1. ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ባይቀርብለትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማንኛውም አይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪነት እንዲቀርብ ማድረግ አለበት፡፡
2. ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት ከያዘው ጭብጥ ውጭ ጭብጡን ለውጦ ፍርድ መስጠት ይችላል፡፡

የመ.ቁ. 13223

ጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - መንበረ አድማሱ ቀረበች

ተጠሪ፡- አቶ አስፋው አበበ - ቀረበ

## <u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ የሥራ ውሌን ከሕግ ውጭ አቋርጦታልና ውዝፍ ደመወዜን ከፍሎ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ሲል በአሁን አመልካች ላይ ክስ መስርቷል፡፡ አመልካቹም ለሥራ ውሉ መቋረጥ ምክንያት የሆነው ተጠሪው ሐሰተኛ ማሕተምና ፊርማ የያዘ የማዘዣ ደብዳቤ ለባንኩ ቀርቦ ሳለ የበኩሉን ማጣሪያ ባለማድረግ የጎንደር ስጋ ፋብሪካ ገንዘብ የሆነው ብር 486,312.00 ለአምጪው በአሰላ ንግድ ባንክ አማካኝነት እንዲከፈል ማድረጉ



መሆኑን በመዘርዘር ባንኩ ኪሣራ ላይ እንዲወድቅ አድርጓልና የሥራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ መቋረጡ ተገቢ ነው ሲል መልሱን ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የደብዳቤው ማህተምና ፊርማ ትክክለኛነት የሥራ ድርሻው በሆነ ሌላ ሰው የተረጋገጠ መሆኑን፣ ተጠሪ ይህን የመስራት ኃላፊነትም ሆነ ግዴታ የሌለበት መሆኑን፣ በባንኩ መመሪያም መሰረት ሰነዱን ከተጠራጠረ ገንዘቡን ከመክፈሉ በፊት አውጪውን ማማከር ያለበት ከፋዩ የአሰላ ባንክ እንጂ ተጠሪው የሚገኝበት የባንኩ የመስቀል አደባባይ ቅርንጫፍ አለመሆኑን በመግለጽ የተጠሪው የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነውና የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ውሣኔው እስከተሰጠበት እለት ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራው ሊመለስ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካቹ ይግባኝ ተጠሪው ደግሞ መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተከራከሩ ሲሆን የከፍተኛ ፍ/ቤትም ተጠሪ የሦስት ወር ደመወዝ ብቻ ተከፍሎት ወደ ሥራ ይመለስ ሲል የስር ፍርዱን አሻሽሎታል፡፡

በመቀጠል አመልካች ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ ተጠሪም መልሱን ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ይህም ችሎት ከቀረበለት ክርክር በመነሳት በጉዳዩ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ተጠሪ ፈጽሞታል በተባለው ተግባር በወንጀል ጥፋተኛ ተሰኝቷል? ወይስ አልተሰኘም? የሥራ ውሉስ መቋረጥ በሕግ የተደገፈ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

#በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና በጥፋቱም ምክንያት ለያዘው ሥራ ብቁ ሆኖ አለመገኘት; የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ምክንያት መሆኑ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/ቀ/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ፍሬ ነገር ስንመለስ አመልካች ተጠሪው በፈፀመው ጥፋት በመ.ቁ. 4176/88 በወንጀል ተከስሶ የጥፋተኛነት ውሣኔ ተሰጥቶበት ብር 500.00 ተቀጥቷል ሲል ተከራክሯል፡፡ ይህ ክርክር የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ አመልካቹ በተጠቀሰው

አይነት ይከራከር እንጂ የወንጀሉን መዝገብ በማስረጃነት ሊያቀርብ አልቻለም በሚል ክርክሩን ውድቅ ማድረጉን በውሣኔው አመልክቷል፡፡

በመሰረቱ አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በእራሱ አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውም አይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪነት ይቀርብለት ዘንድ ማዘዝ እንዲችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.345 ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ እንዲሁም አንድ ፍ/ቤት ለውሣኔው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በእራሱ አነሳሽነትም ሆነ በተከራካሪዎቹ ጠያቂነት በሌላ ፍ/ቤት የሚገኝ ሰነድ፣ የጽሁፍ ማስረጃ ወይም ፍርድ የተሰጠበት መዝገብ እንዲቀርብለት ማዘዝ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.145/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት በአደረገው ምክንያት ሳይገደብ ጉዳዩን እራሱ በተረዳው አይነት ጭብጥ ለውጦ ፍርድ ሊሰጥ እንደሚችል

5

ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 እና 182/2/ ላይ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከኑ [illegible] እንደተመለከተው ይህን ጉዳይ በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪው በወንጀል ተከስሶ የተቀጣ ስለመሆኑ ክርክሩ በአመልካች ቀርቦለታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ክርክሩን ከአዋጅ ቁ. 42/85 አኳያ

ሊመረምረው እና ውሣኔውንም ለመስጠት ተጠሪው በወንጀሉ ጉዳይ የተሰጠበትን የጥፋተኛነት ውሣኔ ይዞት አለያም ጉዳዩ ከሥራ ውሉ መቋረጥ ጋር ያለውን ተያያዥነት እንዲያየው ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ በአመልካች ቁጥሩ የተጠቀሰለትን የወንጀል መዝገብ ከሚገኝበት ፍ/ቤት በእራሱ አነሳሽነት ጭምር ሊያስቀርበው ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ ይህንን አላደረገም፡፡ ይልቁንም ተጠሪው በወንጀል ስለመቀጣቱ ክርክሩ ቢቀርብም መዝገቡ በማስረጃነት ሊቀርብ አልቻለም ሲል ነጥቡን አልፎታል፡፡ በወንጀሉ ጉዳይ የተሰጠው ውሣኔ የሥራ ክርክሩን ጉዳይ ለመወሰን የግድ አስፈላጊ መሆኑ እየታየም ፍ/ቤቱ በወንጀሉ ክስ የተሰጠውን ፍርድ በእራሱ አነሳሽነት አስቀርቦ አለማየቱ የክርክሩን አመራር ከላይ በተጠቀሱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች አለማስደገፉንና በውጤቱም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል ግን ይህ ችሎት ተጠሪው ግብረ አበር በመሆን ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ መጠኑ ከላይ የተጠቀሰው የፋብሪካው ገንዘብ በአሰላ ቅርንጫፍ አማካኝነት ለሌላው ተከሣሽ እንዲከፈል አድርጓል



በሚል ከሌሎች ተከሣሾች ጋር በከባድ አታላይነት ወንጀል በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሶ ፍ/ቤቱ ተጠሪውን በወ/መ/ሕ/ቁ. 412/1/ መሠረት ጥፋተኛ በማድረግ ብር 500.00 የቀጣው መሆኑን እና ይህም ፍርድ በተጠሪው አማካኝነት ይግባኝ በቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 3885 መጽናቱን አረጋግጧል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካቹ በመ.ቁ. 6928 ፍርዱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል ያቀረበውን አቤቱታ በአለመቀበል መዝገቡን የዘጋው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ይህ በወንጀሉ ጉዳይ የተሰጠው ፍርድ ተጠሪው ጥፋተኛ መሰኘቱን ብቻ ሳይሆን ጥፋተኛ የተሰኘው ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ፈጽሞታል በተባለ ወንጀል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የተረጋገጠበት ጥፋትም በስራው ለመቀጠል ብቃት የሌለው መሆኑን ለማሳየት የሚበቃ ነው፡፡ እንደውም የሥራ ውል መቋረጥ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/ቀ/ መደገፉን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም አቤቱታው በቀረበበት ውሣኔ ተጠሪው የሦስት ወር ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራ እንዲመለስ መወሰኑ የሕግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1ኛ. የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው ሕጋዊ በሆነ ምክንያት በመሆኑ ወደ ሥራ ሊመለስ አይገባም፡፡

2ኛ. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 21/88፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ በመ.ቁ. 6222 ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡



ሰበር መ/ቁ. 14414

ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች ፡- የጊምቢ ከተማ አስተዳዳር ጽህፈት ቤት

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ

*ስለ አዋጅ ቁ. 42/85 ተፈጻሚነት - የአሰሪና ሰራተኛ ትርጓሜ - የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 2/1/፣3/2/ /ሠ/*

መ/ሰጭ የአዋጅ ቁ.42/85ን መሠረት በማድረግ አመልካች ይኸንኑ ሕግ ተላልፎ ከስራዬ ያገደኝ በመሆኑ ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት በጊምቢ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበችውን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ መ/ሰጭ ከስራ ከታገደችከት ቀን ጀምሮ ያለው ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ እንድትመለስ አለዚያ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 39፣40 እና 43 የተመለከተው ክፍያ (የስንብትና የካሣ ክፍያ) ተከፍሏት እንድትሰናበት ፍ/ቤቱ በመወሰኑና